የሰበር መ/ቁ. 28508

ኅዳር 5/2000

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

4. አቶ አብዱራሂም አህመድ

5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ የኔነሽ ከበደ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ዮሐንስ ከበደ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ጥር 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ የአሁኑ አመልካች የሥር ተከሣሽ በሆኑበት መዝገብ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የሟች አባታቸው የደጅአዝማች ከበደ ወ/ዮሐንስ የሆነውን ቁጥሩ 375 ቤት አመልካች የያዙ መሆኑን ገልፀው የአመልካችን ድርሻ ¼ ኛ አስይዘው ቤቱን እንዲረከቡ፣ ይህ ካልሆነም ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ እንዲከፋፈሉ የሚል ሲሆን አመልካችም በበኩላቸው ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣ ጉዳዩ ቀደም ሲል የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ነው፣ ተጠሪ ቤቱ የሟች ለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን ያስተናገደው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ያቀረበው የይርጋ ተቃውሞ በወራሽና ያለ ማስረጃ ንብረት በያዘ ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ ተፈፃሚነት ከሚኖረው በስተቀር ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ደግሞ በውል ላይ ለተመሠረተ ግንኙነት የሚጠቀስ እንጂ በወራሾች መካከል የሚጠቀስ በመሆኑ በክርክሩ አግባብነት የለውም፣ ጉዳዩ ቀደም ብሎ የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቷል የተባለውን ሌሎች

ወራሽ ያልሆኑ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡ የተወሰነ ከመሆኑ ውጭ በተመሣሣይ ጭብጥ ላይ የተሰጠ ውሣኔ አይደለም በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞዎች ውድቅ ካደረገ በኋላ ቤቱ የአውራሻቸው ለመሆኑ ካርታው በማስረጃዎች መቅረቡን ገልፆ ክስ የቀረበበትን ቤት ግራ ቀኙ ከተስማሙ አንዳቸው ለአንዳቸው ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ፣ ይህ ካልተቻለ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ የየድርሻቸውን እንዲወስኑ በማለት ወስኗል ውሣኔው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በይግባኝ ፀንቷል አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን አቤቱታው ከተመረመረ በኋላ ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጓ ክርክርራቸውም ከሕግ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት የሥር ፍ/ቤቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000 ላይ የተመለከተው የይርጋ መቃወሚያ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለቱ ውድቅ ማድረጋቸው ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ተመልክተናል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በሚል በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ምክንያት ድንጋጌው በወራሽ እና ወራሽ ሣይሆን ማስረጃ ሣይኖረው ንብረት በያዘ ሰው ላይ ለሚቀርብ ክስ የሚነሣ እንጂ አሁን በወራሾች መካከል ለተነሣው ክርክር ተጠቃሽ አይሆንም የሚል ነው ሆኖም ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች በወ/ሮ ድንቄ ተድላና በተጠሪዎች እነ አቶ አባተ ጫኔ መካከል በነበረው የውርስ ክርክር "በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000/1/ እና 2/ ላይ የሰፈረው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀረብ ነው" በማለት የሰጠውን ውሣኔ ያልተከተለ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ለድንጋጌው የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይርጋ ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው ይገባ ነበር ከተባለ ባጠቃላይ ክርክሩ ላይ ለውጥ ያመጣ ወይም አያመጣ እንደሆነ መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠሪ በንብረት ጥያቄው ላይ ክስ ያቀረበው 20 ዓመት ካለፈው በኋላ ነው በማለት የይርጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጠይቀዋል፡፡ ሆኖም ክስ በቀረበለት ቤት ላይ ቀደም ሲል

በሌላ መዝገብ ክስ አቅርበው ጉዳዩ እስከ ሰበር ደርሶ ከተወሰነላቸው በኋላ የአፈፃፀም መዝገብ ከፍተው ታህሣሥ 21 ቀን 1996 ዓ.ም ቤቱ እንዲረከቡ የአፈፃፀም ትዕዛዝ የተሰጠላቸው መሆኑን በሰበር ማመልከቻቸው ላይ ገልፀዋል፡፡ በሌላም በኩል ያሁኑ ተጠሪ የስር ከሣሽ በመሆን በመልካች ላይ ቤቱን በተመለተ ክስ ያቀረቡት ግንቦት 17 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አኳያ አመልካች ክስ የቀረበበትን ቤት በፍርድ ቤት ውሣኔ በይዞታቸው ሥር በማድረግ የተረከቡት ታህሣሥ 21 ቀን 1996 ዓ.ም. ነው ቢባል እንኳ ተጠሪ በበኩላቸው ክስ ያቀረቡባቸው አንድ ዓመት ተኩል በማይሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ ታይቷል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ እና /2/ ላይ የተመለከቱት የይርጋ ጊዜዎች በ3 እና 15 ዓመት የተካሄዱ በመሆናቸው አመልካች ያቀረቡት የይርጋ ጥያቄ ሁለቱንም ያላሟላ ነው፡፡ ስለዚህ የይርጋ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 53739 ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43795 ጥቅምት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔ በተለየ ምክንያት ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
- ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻቻሉ፡፡
- በትዕዛዝ የመጣው የፌዴራል የመጀመሪያ ደርጃ ፍርድ ቤት መ/ቁ. 53739 የተፈለገበት ምክንያት ስላለቀ ወደመጣበት በሸኚ ደብዳቤ ተመልሶ ይላክ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ